የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ—ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. 44
ADDIS ABABA–6[th] July, 2001

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
የፌዴራል ፍርድ ቤቶች (ማሻሻያ) አዋጅ ........ ገጽ ፩ሺ፮፻፳፬

CONTENTS

Proclamation No. 254/2001
Federal Courts (Amendment) proclamation .......................................... Page 1624

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፬/፲፱፻፺፫

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፬/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፰ (እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· አንቀጽ ፲፰ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፰ ተተክቷል ፤

"፲፰ ስለ ፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ የየፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት፤

፩· ፍርድ ቤቱን ይወክላል ፤ ለዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውክልናና መመሪያ መሠረት የፍርድ ቤቱን ዳኞች ይደለድላል ፤ ሥራ ይሰጣል ፤ ያስተዳድራል ፤

## PROCLAMATION NO. 254/2001

## A PROCLAMATION TO AMEND THE FEDERAL COURTS PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Federal Courts proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Federal Courts (Amendment) proclamation No. 254/2001".

2. *Amendment*

   The Federal Courts proclamation No. 25/1996 (as amended) is hereby further amended as follows:

   1. Article 18 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 18:

      "18. powers and Duties of the presidents and Vice-Presidents of the Federal High Court and first Instance Court.

      A) The president of each Court shall:

         1. represent the Court; without prejudice to the powers and duties entrusted to the Judicial Administration Commission, place, as well as assign and administer judges of the Court pursuant to the delegation and in accrodance with directives given by the President of the Federal Supreme Court.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

